# እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!

## ማስታወቂያ

### የጌታ እራት

የጌታን እራት ፕሮግራም ዛሬ እንካፈላለን። የጌታን ሞት እና ደህንነታችንን ስለምናስብበት ስለዚህ ፕሮግራም እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን። ጌታን እንደ ግል አዳኛችን የተቀበልን ሁሉ እራሳችንን እየመረመርን በዚህ ፕሮግራም እንካፈላለን።

### የአርብ ፕሮግራም

በአርብ ፕሮግራም ዘወትር አርብ ከ7 p.m. ጀምሮ እየተገናኘን እንጸልያለን። ቃሉንም እንማራለን። በዚህ ፕሮግራም ላይ በመገኘት የበረከቱ ተካፋዮች እንድንሆን ሁላችንም እንድንሳተፍ ቤተ ክርስቲያን ታበረታታለች። በተለያየ ጉዳይ እንዲጸለይላችሁ የምትሹም አገልጋዮችን ማነጋገር ትችላላችሁ። ጌታ ይባርካችሁ!

"ወደ ውጭም አውጥቶ:- ጌቶች ሆይ፥ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? አላቸው።
እነርሱም:- በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት።" (ሐዋ. 16፡ 30-31)



- ⇒ የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ በምጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?
- ⇒ ማገልገል ይፈልጋሉ?
- ⇒ Yeec.org App ጭነዋል?
- ⇒ http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?

ሽማግሌዎችን ለማግኘት:-
773-886-0818 (ወ/ም ሲሳይ)
773-507-0194 (ወ/ም አያሌው)
773-910-0485 (ወ/ም ፒተር)
773-961-5332 (ወ/ም ጌቱ)
773-739-0437 (ወ/ም ሰለሞን)

### መደበኛ ፕሮግራሞች

እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን

Chicago Yemsrach Evangelical Church

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2፡10




"...እመን ብቻ እንጂ አትፍራ..."
(ማር. 5፡36)


Chicago Yemsrach Evangelical Church
4455 N. Seeley Avenue
Chicago, IL 60625



መደበኛ ፕሮግራሞች

እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.


January 21, 2018 | ጥር 13፣ 2010 ዓ.ም.

## የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

| | |
|---|---|
| ጸሎት መሪ................ | ወንድም ጴጥሮስ መኩሪያ |
| አምልኮ...................... | የቤተክርስቲያን አምልኮ ቡድን |
| ፕሮግራም መሪ .......... | ወንድም ጴጥሮስ መኩሪያ |
| ቃል ............. | ወንድም ዘሪሁን ዳዊት |
| ማጠቃለያ ................. | ፕሮግራም መሪ |

### የሳምንቱ ጥቅስ

"የሰማይ አምላክ ለዘላለም የማይፈርስ መንግሥት ያስነሣል፤ ለሌላ ሕዝብም የማይሰጥ መንግሥት ይሆናል፤ እነዚያንም መንግሥታት ሁሉ ትፈጫቸዋለች ታጠፋቸውማለች፥ ለዘላለምም ትቆማለች።"

(ዳን. 2፡ 44)

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች**

| መሪ | ቀን | አድራሻ |
|---|---|---|
| ወ/ም አያሌው አሰፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሐሙስ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| ወ/ም ሰለሞን ወመን | ቅዳሜ | 549 Sheridan Rd., Apt. 3, Evanston, IL 60202 |
| ወ/ም መስፍን ጌታቸው | ዕሮብ | 4631 N. Beacon St., Chicago, IL 60640 |

## መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

**ጸሎት አስተምረን -- መንግስት ለዘላለም የእግዚአብሔር ነው (ክፍል አስራ-ስድስት)**

*"እንግዲህ እናንተስ እንዲህ ጸልዩ፡- በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ... መንግሥት ያንተ ናትና ኃይልም ክብርም ለዘለዓለሙ፤ አሜን።" (ማቴ. 6፡13)*

ከዚህ በፊት እንዳየነው በመንፈሳዊው አለም ሁለት መንግስታት አሉ። የእግዚአብሔር መንግስት አለ፤ የሰይጣን መንግስት አለ። በሉቃስ 12 ላይ እንደምናነበው ፈሪሳውያን ጌታን "በብዔል ዜቡል በአጋንንት አለቃ" አጋንንትን ያወጣል በማለት ከሰሱት። ጌታ ግን አሳባቸውን አውቆ "እርስ በርስዋ የምትለያይ መንግሥት ሁሉ ትጠፋለች ... ሰይጣንም ሰይጣንን የሚያወጣ ከሆነ፥ እርስ በርሱ ተለያየ፥ እንግዲህ መንግሥቱ እንዴት ትቆማለች?... እኔ ግን በእግዚአብሔር መንፈስ አጋንንትን የማወጣ ከሆንሁ፥ እንግዲህ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ ደርሳለች።" (ቁ. 25፣ 26፣ 28) በዚህ ስፍራ በግልጽ እንደምናነበው ሰይጣን የሚሰራበት የጨለማ መንግስት አለ። ደግሞም የእግዚአብሔር ሃሳብ የሚከናወንበት የእግዚአብሔር መንግስት አለ። የሰይጣን መንግስት ከእግዚአብሔር መንግስት ተጻራሪ የሆነ የከፋት መንግስት ነው።

የመንግስታት ግንኙነት የኃይል ግንኙነት ነው። አንድ መንግስት ተጽንኦ በሚያሳድርበት ስፍራና ሁኔታ ሌላ መንግስት ተጽንኦ ማሳረፍ አይችልም። የእግዚአብሔር መንግስት በኃይል በምትሰራበት ስፍራ የጨለማው መንግስት መስራት አይችልም። የግዚአብሔር መንግስት የብርሃንና የጽድቅ መንግስት ስልሆነ የጨለማ ኃይል በፊቱ ሊቆም አይችልም። ስለዚህ የጌታ መንፈስ ባለበት ስፍራ ሁሉ አርነት አለ። ስለዚህ ነው የእግዚአብሔር መንግስት በምትገዛበት ስፍራ ሁሉ ሰዎች ከተለያየ እስራት የሚፈቱት። መንፈስ ቅዱስ በሚሰራበት ስፍራ የሚገለጠው የእግዚአብሔር መንግስት ነው። ጌታችን "እኔ ግን በእግዚአብሔር መንፈስ አጋንንትን የማወጣ ከሆንሁ፥ እንግዲህ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ ደርሳለች" ብሎናል። (ማቴ. 12፡28) አጋንንት ሰዎችን ለቀው የሚወጡት ከእነርሱ በሚበልጥ ኃይል ብቻ ነው። ያም ደግሞ የእግዚአብሔር መንግስት ኃይል ነው። ቤተ ክርስቲያን በምድር የእግዚአብሔር መንግስት መገለጫ ስለሆነች የገሃነብ ደጆች አይችሏትም። ያቆማትና የሚደግፋት ብርቱ የሆነው የእግዚአብሔር መንግስት ኃይል ነው።

የአባታችን ሆይ ጸሎት የሚፈጸመው መንግስት ለዘላለም የእግዚአብሔር እንደሆነ በማወጅ ነው። ምንም እንኳ አሁን በምንኖርበት አለም የተለዩ መንግስታት ቢኖሩም፤ እንዲሁም ምንም እንኳ አሁን በክፉ የሚገለጥ የጨለማ መንግስት ቢኖርም፤ መንግስት ግን ለዘላለም የእግዚአብሔር ነው። መጽሐፍ ቅዱሳችን እንደሚያስተምረን በመጨረሻ "የሰማይ አምላክ ለዘላለም የማይፈርስ መንግሥት ያስነሣል፤ ለሌላ ሕዝብም የማይሰጥ መንግሥት ይሆናል፤ እነዚያንም መንግሥታት ሁሉ ትፈጫቸዋለች ታጠፋቸውማለች፥ ለዘላለምም ትቆማለች።" (ዳን. 2፡ 44) በመጨረሻ ሰይጣንና መንግስቱ ከጭፍሮቹ ጋር በእሳት ባሕር ይጣላሉ። (ራዕ. 20፡10) አባታችን ሆይ መንግስት ለዘላለም ያንተ ብቻ ነው። አሜን!